# የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ከሰብዓዊ መብት መከበር አኳያ

**ብርሃኔ ይኸይስ**

ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለማንሳት የወደድኩት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የአሜሪካው ስቴት ዴፓርትመንት ዓመታዊ ሪፖርትን ተከትሎ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጉዳዮች የሚዲያው ሰሞንኛ አጀንዳዎች መሆናቸውና የሚወጡት ዘገባዎች እና የስቴት ዴፖርትመንቱ ሪፖርት ምን ያህል ይገልጹናል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት በአለም ኢኮኖሚ ፎረም ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዴሞክራሲንና ልማትን በተመለከተ የተናገሩትን ተንተርሶ የነበሩት ዘገባዎች ሲሆኑ፤ ይህን የጠቅላይ ሚኒስትሩን አስተያየት ተከትሎ ያለዴሞክራሲ ልማት የለም የሚሉትን እና ለዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መጎልበት ኃላፊነቱ የመንግስት ብቻ እንደሆነ ለሚገልፁቱ ተጫባጩን የሃገሬ ሁኔታ በተመለከተ ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች አንፃር የወፍበረር ቅኝት ማድረግ ነው፡፡

በአፍሪካ በአጠቃላይና በአገራችን ሁኔታ ህዝቦች በማእከላዊ መንግስት በተወሰነው ቋንቋ/ እምነት እንዲዋጡ ስትራቴጂ ሲነደፍ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉት የዴሞክራሲ ሁኔታ፣ የኢኮኖሚ እድገትና የሰብአዊ መብት መከበር ጭራሽኑም ያልነበሩ በመሆናቸው በቀላሉ ለጦርነት የሚያመች ሁኔታ መፈጠሩን እናስታውሳለን፡፡

የዚህ ውጤት በአብዛኛው የአገራችን ክፍል የሚገኙ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋ፣ ባህልና እምነት መረገጡና ፍትሃዊ የሆነ የሥልጣንና የሃብት ክፍፍል ባለመኖሩ ምክንያት ረዥም ጊዜ ወደወሰደው ጦርነት መግባታችን ነው፡፡ ስለሀገራችን ፖለቲካ ከእኛ በላይ ያገባናል የሚሉ ምዕራባውያንና የነሱን አመለካከት የሚያራምዱ የሀገሬ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ አንዳንድ የግሉ ፕሬስና ጥቂት ምሁራን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር ስልጣንና ሃብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ያለመከፋፈል እንጂ የብሄር፣ የእሴቶች /ቋንቋ ባህል/ ወዘተ ግጭት ተደርጎ መወሰድ የለበትም ሲሉ ይጽፋሉ፣ ይከራከራሉ፡፡

እንደነዚህ ፀሃፊዎችና ተከራካሪዎች አመለካከት ከሆነ ብሄር/ እምነት ግጭት የሚባል እንደሌለና ይልቁንስ በብሄር/ እምነት ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች (Political Elites) ዋና አላማቸውና ግባቸው ስልጣንና ሀብት መቆጣጠር እንደሆነ፣ ለግጭት ምክንያት እንደሆነ የሚወሰደው የቋንቋ/ ሃይማኖት ወዘተ ጉዳይ ፍትሃዊ የሆነ የሃብትና የስልጣን ክፍፍል ሲደረግ እንደጉም ተኖ እንደሚጠፋ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በታቃራኒ የሚከራከሩ ምሁራን እንደሚሞግቱት ግን ከላይ የተገለጸውን አመለካከት ተግባር ላይ ያዋሉ ምዕራባዊያን ቢያንስ በሃገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ ሲደርሱና ገዢ ፓርቲዎችም ሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለዚህ ስትራቴጂ አጋዥ ሊሆኑ በሚችሉት የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ እንዲሁም በሰብአዊ መብት መከበር ላይ ተመሳሳይ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸውና በርትተው በመስራታቸው ነው ይላሉ፡፡

ስለሆነም ምሁራን መሰረታዊ በሆኑ አገራዊ አጀንዳዎች ላይ አንድ አይነት አቋምና አበርክቶ ለነበራቸው ምዕራባውያን ከቋንቋ ባህልና ዕምነት ይልቅ ለስልጣንና የሀብት ክፍፍል ትኩረት መስጠታቸው በነሱ አውድ ጤናማ ቢሆንም በኛ ሁኔታና ባጠቃላይ ስለአለማችን እያሰብን ከሆነ ግን ቋንቋዎችና እምነቶቹ እንደጉም ተነው ይጠፋሉ የሚለው አመለካከት ብዙም ሩቅ የማያስኬድ ነው ይላሉ፡፡ በማሳያነትም እንደ ህንድ ስዊዝ ቤልጅየምና ካናዳ ያሉ ከእኛ በብዙ ሁኔታ በተለይም በዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሱትና ለብዙ ክፍለ ዘመናት በሰላም የኖሩት አናሳ ህዝቦች እየጠፉ በመምጣታቸው ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ መብታቸውን ለማስከበር የተሻለ ሥርዓት መፍጠር በመቻላቸው እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

ስለዚህም የኢኮኖሚ እድገት ወይም የዴሞክራሲ ማበብ በራሱ ግጭት ለመቀነስ ጠቃሚ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱትን ያደጉ ሀገሮችን ጨምሮ በእኛና በሌሎችም ሕብረብሄር በሆኑ አገሮች ህዝቦች በልዩነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ለመመስረት የሚያደርጉት ትግል የህልውናና የማንነት ጥያቄ ጭምር እንጂ የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ዕድገት ጥያቄ ብቻ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

እንደሚታወቀው ሕገ መንግስቱ በዋናነት ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያለመ ነው፡፡ አንደኛው ለዘመናት የግጭት ምክንያት የሆነውን ስልጣንና ሀብት በማዕከልና በጥቂት ሃይሎች መከማቸት የፈጠረውን ችግር መመለስ በሀገራችን ተጫባጭ የማህበረ ፖለቲካ ሁኔታ የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ስልጣንና ሀብት በፌደራል እና በክልሎች መካከል መከፋፈሉ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የህዝቦችን የማንነት ጥያቄ ለመመለስ ህዝቦች ራሳቸውን የማስተዳደር የራሳቸውን ማንነት፣ ቋንቋ፣እምነትና ታሪክ ለማሳደግና ወደ ቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡

እነዚህ ባልተመለሱበት ሁኔታ አሁን አሁን የምዕራባውያንን ተሞክሮ እንዳለ መቀበል አለብን የሚሉት ፓርቲዎችና ሚዲያዎች በተቃራኒው ሃሳባቸው ሁሉ እንደጉም የሚተን ስለመሆኑ ምሁራኑ አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡ ስለሀገራችን ፖለቲካ ጉዳይ የሚከራከሩ የውጭ ሃይሎችም ሆኑ የውስጥ ተቀዋሚ ፓርቲዎች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፀር ነው ሲሉ ከሚያወሱት ህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም ባሻገር በሁለተኛነት የሚጠቅሱት ጉዳይ የሰብአዊ መብት ጉዳይን ነው፡፡ በተለይም ይህን መብት ብዙ ጊዜ የሚያነሱት ከምርጫ ፖለቲካ ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ስለሆነም ስለምርጫና ሰብአዊ መብት

ስንነጋገር በዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መካከል ያለውን ግንኙነት የመዳሰስና እውነታውን የማመላከት ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው፡፡

እስከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ድረስ አንድ አገር ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነትን ብትፈርምም በየሀገራቱ መካከል በነበረው አንዱ በሌላው ላይ ጣልቃ ያለመግባት ግዴታና የአገሮች የፖለቲካ ሉዓላዊነት ጉዳይ ሰፊ ቦታ ይሰጠው ስለነበር በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሰረት ለዓለም ሰላምና አለመረጋጋት ጠንቅ ሆነዋል ካልተባለ በስተቀር አለም አቀፍ እርምጃ ይወሰድ የነበረበት ሁኔታ ውስን ነበር፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ግን ባይሳካም በሱማሊያና ቀድሞ ዩጎዝላቪያ እንደታየው አይነት ሰብአዊ ቀውስ “humanitarian Crisis” አለ ብሎ ካመነ ዓለም አቀፍ ማህብረተሰብ ጣልቃ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ መታየቱን ተመራማሪዎቹ በዋቢነት ያነሳሉ፡፡

ከዚህ ውጭ የተለየዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች የተለያዩ ኮሚቴዎች በማቋቋም አገሮች ያለባቸውን ግዴታ እንዲወጡ የተለያየ ተጽእኖ የሚያደርጉ ቢሆንም ተጽኗቸውና እርምጃቸው ግን መሰረታዊውን የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መርሆ መሰረት ያደረገ ሳይሆን “የጠላሁትን ጥሉልኝ እና የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” የሚለውን ብሂል መሰረት ያደረገ እንደሆነ ብዙዎቹ ሀገራት የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

ዶክተር አሰፋ ፍስሃ የተባሉ የፖለቲካ ምሁር ጥር 2002 ዓ.ም ላይ "ምርጫና ሰብአዊ መብት" በሚል ባቀረቡት አንድ የጥናት ወረቀት ላይ እንደሚያወሱት በአንድ አገር ላይ ሰብአዊ መብቶች መሰረት እንዲይዙ ወይም እንዲጸኑ ቀዳሚው ሃላፊነት የሚያርፈው በአገሪቱ ፍርድ ቤቶች፣ ሰብአዊ መብት ኮሚሽኖች እምባ ጠባቂና ሌሎች ተቋማት ላይ ነው፡፡ ይህ ተፈጻሚ ባልሆነበት ሁኔታ ብቻ ነው ዓለም አቀፍ ተቋማት ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉት የሚለው አስተሳሰብ ሰፊ ስፍራ ይዞ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሁሉም ዓለም አቀፍ ሰነዶችና በአብዛኞቹ ሀገራት ህገ መንግስቶች ውስጥ በመብቶች ላይ የተወሰነ ገደብ ሊኖር እንደሚችልና ይህም ተገቢ እንደሆነ  የዶክተር አሰፋ ፍስሃ የምርምር ውጤት ያብራራል፡፡

ጥናቱ በጉዳዩ ላይ ዝርዝሩን ሲቀጥል አንደኛ አንድ መብት የሌላ ሰው መብት ለማክበር ሲባል የተወሰነ ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል፤ ሁለተኛ መንግስት በምክር ቤት በፀደቀ ህግ እና ለተወሰነ ዓላማ እንዲሁም በአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊፈቀድ የሚችል ገደብ ሊጥል የሚቻልበት አሰራር በሁሉም ሀገራት መኖሩ ይታወቃል ይላል፡፡ ለምሳሌ የሃገር ደህንነትና ፀጥታ አደጋ ላይ ሲሆን፣ በጦርነት ጊዜ፣ የሌሎችን መብት ለማክበር፣ የዜጎችን ሞራልና ክብር ለመጠበቅ ሲባል ይኸው ሊደረግ እንደሚችል እና ይህም እየተተገበረ ካሉባቸውን ሀገራት መካከል ጥቂቶቹን  ሰነዱ ይጠቁማል፡፡ የሀገራችንን ህገመንግስት  ስንመለከትም ገደብ የሚጣልበትን  አግባቦች  በግልጽ ያመለክታል፡፡

ሆኖም ብዙዎች የሀገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አንዳንድ የግል ጋዜጦች መብታቸው እስከየትኛው ጥግ እንደሆነ ለመመልከትና ግዴታቸውንም ለማጤን ፍላጎት ያላቸው አይመስልም፡፡ ስለሆነም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የ"መብታችን ተጣሰ" ጥያቄና አቤቱታ ለውጭ ሃይሎች ያቀርባሉ፤ በየጋዜጣውም ይጽፋሉ፡፡ ለምሳሌ ጋዜጦቹ ስለፕሬስ ነጻነት በህገመንግስቱ በግልጽ የተቀመጠውን አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ የሚቀበሉት በንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 የተቀመጡትን ገደቦች ወደጎን በመግፋት ነው፡፡

በዚህም ምክንያት ይመስላል አብዛኞቹ የግል ጋዜጦች የአመጽ ጥሪዎችን፣የግለሰቦችንና ተቋማትን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፉ ዘለፋዎችን፤ የህብረተሰቡን ሰላምና ወግ ፣ባህልና ልማድ የሚንዱ፣ የወጣቱን ሞራል የሚነኩ ጽሁፎችን በማተም ላይ የሚገኙት፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከላይ በጭፍን ተቃውሞ የተሰለፉትና ገደቦችን ከማያስተውሉት ጋዜጦች የሚደርስባቸውን ውግዘትና ተጽእኖ በመፍራት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከገበያ ጋር በተያየዘ ምክንያት በአጥፊዎቹ ወይም የህግ የበላይነትን በሚጻረሩት ጋዜጦች መንገድ እየተጓዙ ነው፡፡

ይህን ጉዳይ በጥንቃቄ መርምሮና ፈትሾ አስተያየት መስጠት የሚገባው አካል በተለይም በአለም አቀፍ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ላይ የተሰማሩቱ  ተቋማት ስለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ሰብአዊ መብት መከበር ጽኑ አቋም ካላቸው በትክክል መመርመር፣ መፈተሽና የተስተካከሉ ጉዳዮች የሚቀጥሉበት፣ በነበሩበት ያሉት ደግሞ የሚታረሙበት ሁኔታ እንዲፈጠር ድጋፍና ተጽእኖ ማድረግ ሲገባቸው ከላይ የተገለጹትንና ከህግ የበላይነት በተፃራሪው የተሰለፉ ሃይሎችን አቤቱታ ብቻ በመቀበልና በምንጭነት በመጠቀም የሚያወጡት ሪፖርት የትም አያደርስም፡፡

ሪፖርታቸው ትክክል እንኳ ሆኖ ቢገኝ ከተቋቋሙበት አላማ አኳያ መቅደም የሚገባው መልካም አፈጻጸሞችን እውቅና በመስጠት መታረም የሚገባቸውን ደግሞ በትክክልኛና ሚዛናዊ መረጃ አስደግፎ ገንቢ አስተያዬት መስጠት ሲገባ እነርሱ የሚደግፉትን የአንድን ወገን ፍላጎት ለማሟላት ብቻ ታስበው የሚወጡ /ለዚያውም ለተሳሳተው ወገን በግልጽ የሚያደሉ/ ወገንተኛ ሪፖርቶች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህ ደግሞ የየሀገራቱን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከማጎልበትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ይልቅ  ሂደቱ እንዲቀጭጭ ያደርገዋል፡፡

ይህን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የሀገራችንን የሰብአዊ መብት አያያዝ ጤናማ ለማድረግ በአለም አቀፍ ደረጃ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ሀገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የሰብአዊ መብት እና እንባ ጠባቂ ተቋማት የሰሩትን ስራና የደረሱበትን ድምዳሜ በምንጭነት ለመውሰድ እና ለማነፃፀር እንኳ ያልፈቀደው የሰሞኑ የስቴት ዲፓርትመንት ዓመታዊ ሪፖርት በአንፃሩ ግን ምንም እንኳን ጅምላ እና አሳማኝ ምንጭ ባይሆኑም የተቃዋሚ ፓርቲዎችና አመራሮች፤መያዶች እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜው ቅሌታቸው ይበልጥ እየተገለጸ የሚገኙትን የሂውማን ራይትስ ዎች

/HRW/ የመሰሉ ተቋማትን በዋቢነት መጠቀሙ ከላይ በተገለጸው የሰብአዊ መብት መርሆ መሰረት በስቴት ዲፓርትመንት የሚገኙ የአንዳንድ ባለሥልጣናትና ኃላፊዎች የግል አካሄድና አመለካከት ሁሉ እሾሃማና ስውር መሆኑን ያመለክተናል፡፡

ዴሞክራሲ ስንል ረዥም ዘመን ያለውና ህዝቡ በተወካዮቹ አማካይነት በማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በቀጥታ የሚሳተፍበት፤የራሱን ጉዳይ በራሱ የሚወስንበት አሳታፊ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተለያዩ የጥናት ሰነዶች እንደሚጠቁሙት እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ አሁን በዴሞክራሲ ባህላቸው አደጉ የምንላቸው አገሮችም ጭምር አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ማለትም ሴቶችን፣ የተጨቆኑ የህብረተሰብ አባላትን፣ ከዚህም ባለፈ ጥቁሮችንና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ዜጎችን ወዘተ ያላካተተና በግምት 40 ከመቶ የሚሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ያገለለ ነበር፡፡ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ግን ይህ ተቀይሮ በብዙ የአለማችን ሀገራት ደረጃውና አፈጻጸሙ ይለያይ እንጂ ከነጉድለቶቹ በአመዛኙ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበትና ወኪሎችን በየጊዜው የሚመርጥበት ሥርዓት እውን እየሆነ መጥቷል፡፡

ይህ አጠቃላይ መነሻ ሁሉንም የዴሞክራሲ ሥርዓት እንከተላለን የሚሉ ሃገሮችን የሚገልፅ ቢሆንም ዴሞክራሲ ሲባል አንድ ወጥ የሆነና ሁሉንም የሚያስማማ ሃሳብ ነው ማለት እንደማይቻል የሚገልጹት ሰነዶች አንድን ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ነው ለማለት እንደመመዘኛ ጥቅም ላይ የሚውሉ በርከት ያሉ መሰረታዊ ነጥቦች መኖራቸውን ይገልጻሉ ። ከነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የተያያዘውና የሰብአዊ መብት ተቋማት፣ ስቴት ዲፓርትመንት፣ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አጠቃላይ የግሉ ጋዜጣ ከሀገራችን ዴሞክራሲ ጋር በማያያዝ የሚያነሱት ጉዳይ በዋናነት ከምርጫ ጋር የተያያዘውን በመሆኑ ሰነዱ ካስቀመጣቸው መገለጫዎች ውስጥ ይህንኑ መሰረታዊና በአንደኛ ደረጃ የተቀመጠውን ምርጫና ዴሞክራሲን የተመለከተውን ጉዳይ አነሳለሁ፡፡

እንደሚታወቀው የዴሞክራሲና የምርጫ ሂደቶች ፍትሃዊነት ከሚለካበት ቁልፍ መለኪያዎች አንዱና መሰረታዊው ነገር የሚካሄደው ምርጫ ሁሉን አቀፍ የመሆኑ ጉዳይ ነው (inclusiveness)፡፡ ይህ ማለት በእማሬያዊ ፍቺው ወይም ላይ ላዩን ሲታይ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ግለሰብ አገሪቱ የምትከተለውን “የጨዋታ ህግ” እስካከበረ ድረስ በአመለካከት፣ በፆታ፣ በሃይማኖት ወዘተ ምክንያት እንዳይገለልና በሂደቱ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ ላይ ያተኮረ ቢሆንም፤ጽንሰ ሃሳቡ ወይም ፍካሬያዊ ትርጉሙ ከዛም የገዘፈ ትልቅ መልዕክት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በተለይም እንደኛ ካሉ የተለያዩ ቋንቋና እምነት ያላቸው ህዝቦች እንዲሁም ለረዥም ዘመን ከቆየ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ሌሎችን አግልሎ ስልጣን የተቆጣጠረበት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ “inclusiveness” በምርጫ ሂደት ብቻ ሳይወሰን ምርጫ ከተጠናቀቀም በኋላ በሚኖረው የፖለቲካ ሂደት ፣ከመድረክና የተቋሞች ግንባታ የዘለቀ ስራ መሰራት እንዳለበትም ጭምር የሚያስገነዝብ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ እንደኛ ያሉ የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት ወዘተ ያላቸው ህዝቦች የሚያጋጥማቸውን “Legitimacy Crisis” መልስ በመስጠት ረገድ “inclusiveness” አይነተኛ መፍትሄም ጭምር እንደሆነ አብዛኞቹን የአለማችን ፖለቲከኞች ያስማማ ጉዳይ ነው፡፡

ይህን አስተሳሰብ የስነ አይምሮ ጠቢባን ከጋራ (group) ፎቶ ጋር አያይዘው ይገልጹታል፡፡ አስር ሰዎች በጋራ ፎቶ ቢነሱና ፎቶው ከታጠበ በኋላ ለእያንዳንዳቸው ሲሰጥ ሁሉም በመጀሪያ የሚያዩት የራሳቸውን ፎቶ እንደሆነና፣ ይህን ካደረጉ በኋላ ብቻ ቀጥለው የሌሎችን ምስል ማየት እንደሚጀምሩ ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መንግስትን በጋራ እንደተነሳ አንድ ፎቶግራፍ ወስደን ብናየው እያንዳንዱ ዜጋ ብሄር/እምነት ወይም የፖለቲካ ድርጅት ምስሉ በጋራ ፎቶግራፉ ላይ እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ፎቶግራፉን ለመመልከት ያን ያህል ፍላጎት አያሳይም፡፡

ከዚህ አንፃር በእኛ ሀገር የተዘረጋውን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ከምርጫና ውክልና አንፃር ስንመለከተው ከላይ የተገለጸውን አለም አቀፋዊ መስፈርት አሟልቶ እናገኘዋለን፡፡ ታዲያ ለምን? ሁሌም ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ “የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች” በገዢው ፓርቲ ላይ ተመሳሳይ ይዘት ያለው አቤቱታና ኡኡታ ያሰማሉ? ችግሩ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ ፓርቲዎች ሊኖራቸው ከሚገባው ሚና የሚመነጭ እንደሆነ አብዛኞቹ የፖለቲካ ምሁራን ይስማማሉ፡፡

ስለ እውነት ለመናገር በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ ድርጅቶች በመንግስት ደረጃ እውቅና አግኝተው ዜጎችም በነፃነት የፖለቲካ ፓርቲ በመመስረት በፖለቲካ ሂደቱ መሳተፍ የጀመሩት ከ1983 ወዲህ መሆኑ ብዙዎቻችንን የሚያስማማ ጉዳይ ነው፡፡ አራት አመት የፈጀ የሽግግር ወቅት ከተደረገ በኋላ ከ1987 እስካሁን ድረስ ደግሞ አራት አገር አቀፍና ክልላዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህን አራት አገር አቀፍ እና ክልላዊ ምርጫዎችን ከዴሞክራሲና ከህብር ፓርቲ መርሆ ጋር አገናኝተን ብንመረምር የተቃዋሚ ፓርቲዎቻችንን አሉታዊ ሚና ለመረዳት እንችላለን፡፡

በተለያየ ጎራ ተሰልፈው የሚገኙት እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደተቋም ሳይሆን በግለሰቦች እና በጥቂት መሪዎች የሚሽከረከሩ ከህዝብ ጋር ጠንካራ ትስስር ያልፈጠሩ በመሆናቸው ምክንያት ገዢውን ፓርቲ በሚፈታተን መልኩ መወጣት አለመቻላቸው ለዴሞክረሲያዊ ስርዓት ግንባታው አስቸጋሪ ሁኔታ ነው፡፡

በተጨማሪም አሰራራቸው ዴሞክረሲያዊ አለመሆኑና እንወክልሃለን የሚሉትን ህዝብ ጥቅም ወደጎን በመተው የራሳቸውን የግል ወይም የቡድን ተልዕኮ ለማሳካት መንቀሳቀሳቸው ከህዝቡ ጋር ያላቸውን ትስስር እንዲዳከም ያደረገው በመሆኑ በዚህም በኩል ሚናቸውን ምንም እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍኖ የምናየው የፖለቲካ አስተሳሰብ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ማለት ገዢው ፓርቲ የያዘውን ፖሊሲ መቃወም ብቻ የሚመስላቸው ሃይሎች የመኖራቸው ሁኔታ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሕዝብ ከተመረጡ ነገ የመንግሥት ሥልጣን ተረካቢ የመሆን እድል ያላቸው ከመሆናቸው አንፃር ገዢውን ፓርቲ ከመቃወምና ከማብጠልጠል አልፈው ዘርዘር ያለና የሕዝብን ጥቅም የሚያረጋግጥ አማራጭ ፖሊሲና የነጠረ ሕዝባዊ አመለካከት ለህዝቡ መሸጥ ይገባቸዋል፡፡ አለበለዚያ ግን  ከዚህ አይነት ጭፍን አስተሳሰብ ያልተሸጋገሩት የፖለቲካ ሃይሎች ስልጣን ቢይዙስ ምን ያህል የተረጋጋና ዘለቄታዊነት ያለው የፖለቲካ ሥርዓት ይኖረናል? የሚለውን ጥያቄም አብሮ ማሰቡ የግድ ይለናል፡፡

ከሁለተኛው ችግር ጋር ተያየዥነት ያለው ሆኖም ግን በራሱ እንደምክያት ጎልቶ መውጣት ያለበትና በተለያዩ ጎራ የሚገኙ የፖለቲካ ሃይሎች የሚያሳዩት አደገኛ አመለካከት ገዢውን  ፓርቲ ለማድከም ሲባልና በህዝቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት (legitimacy) ለመቀነስ የተከተሉት ስትራቴጂ (ከሽግግር ዘመኑ ጀምሮ ማለት ነው) ምርጫ በተቃረበ ቁጥር አልፎ አልፎ ከሂደቱ ራሳቸውን ማግለልና ደጋፊዎቻቸው እንዳይሳተፉ ቅስቀሳ ማድረግ፣አለያም የምርጫውን ትክክለኛና ሕጋዊ አካሄድ ማጣጣል፣በምርጫ 97 ደግሞ ያገኙትን ድምጽ ዋጋ በማሳጣት ፓርላማ አንገባም በማለት የፖለቲካ ሂደቱን ለማዳከም መሞከራቸው እንደ አንድ ችግር መጠቀስ ያለበት ነው፡፡ ይህ አካሄድ በለሎች ታዳጊ ዲሞክራሲ ባለባቸው ሀገሮችም የሚታይ ነው ቢባልም በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ገኖ የሚታይ ችግር መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቋቋሙበት ዋና ምክንያት/ዓላማ ደጋፊያቸውንና አባላቸውን በአንድ የፖለቲካ ዓላማ ስር በማደራጀት፣ በማስተማርና በመምራት በምርጫ ጊዜ ወሳኝ ሆነው መውጣትና በሕዝብ ምርጫ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ ነው፡፡ ሆኖም በየጊዜው  ምርጫ በተቃረበ ቁጥር በአመዛኙ የምናየው ሂደቱን የመኮነንና ብሎም በተለያዩ መንገዶች ለማሰናከል መጣር ሲሆን፣ ይህም ታዲያ ቢያንስ ቢያንስ እንወክልሃለን ከሚሉት የህብረተሰብ ክፍል ጥቅምና እንዲያም ሲል ከአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት መጎልበት አንፃር ታላቅ ጉዳት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለዚሁ በተደጋጋሚ የሚቀርበው መልስ የፖለቲካ ምህዳሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጥበብና በክልሎች አካባቢ የተመቻቸ የፖለቲካ ሁኔታ አለመኖሩ ነው፡፡ ይህ  ሰበብ እውነትም ብቸኛ ምክንያት ከሆነና የተወሰነ እውነትነት ካለው ገዥው ፓርቲ የዲሞክራሲ ሥርዓቱ ሁሉን አቀፍ እንዲሆንና ስር እንዲሰድ  በክልሎች አካባቢ የሚታየውን አንዳንድ ችግር በጊዜ መፍትሄ በመስጠት የዲሞክራሲ ሂደቱ እንዲጎለብት የማድረግ ሃላፊነት አለበት እላለሁ፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን በሂውማን ራይትስ ዎች እና በስቴት ዲፓርትመንት መግለጫ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት አንችልም።